

# ደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤት ክርስቲያን
# የ2021 ዓመታዊ ሪፖርት
# September 4th, 2022

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ**

***<u>የደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን  መንፈሳዊ አገልግሎት ሪፖርት</u>***

***መንፈሳዊ አገልግሎቱ የሚከተሉትን ያጠቃልላል***

**1.ጸሎተ ቅዳሴ**
**ዘወትር እሁድ መደበኛው  አገልግሎት ሳይቋረጥ ለምእመናን ተሰጥቶአል በወረርሺኙ ሰዓት ቆራቢዎችና ባለ ክርስትናዎች እየተመዘገቡ  ተስተናግደዋል**

**2.ስብከተ ወንጌል**
**ስብከተ ወንጌል በየሳምቱ እሁድ  እሁድ በየወሩ ለኪዳነ ምሕረትና አማኑኤል ከተለያየ የአሜሪካ  ስቴት ከካናዳና ከአገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ መምህራን ተሰጥቶአል**

**3.የክርስትና  ሥርዓተ ጥምቀት**
**የክርስትና  ሥርዓተ ጥምቀት በወረርሺኙ ወቅት ቤተሰቡን  ብቻ እየመዘገብን  በማንኛውም ሰዓትና ዕለት በጠየቁ ጊዜ ሁሉ አገልግሎት ተከናውኖአል**

**4.ጸሎተ ፍትሐት**
**ከዕለት ሞት አንስቶ  እስከ 30-40ና 80 ቀን ሙት ዓመት  መታሰቢያ ፍትሐት አድርገናል**

**5.የልጆች ትምህርት**
**ዘወትር ቅዳሜ ልጆችን ከፊደል ጀምሮ እስከ ግብረ ድቁና ተሰጥዎ አስተምረን ቤተ ክርስቲያኑን የሚያገለግሉ ዲያቆናትን አድርሰናል**

**6.የምክር አግልግሎት**
**ምእመናን በተለያየ ጊዜ በተለያየ ምክንያት ምክር ትምህርትና ቡራኬ በአካልና በዙም አገልግሎት ሰጥተናል**

**ውስብሐት ለእግዚአብሔር**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

## <u>በሰበካ ጉባኤ አስተዳደር የተከናወኑ እና የተወሰኑ የ2021 ዋና ዋና ጉድዮች</u>

የሰበካ ጉባኤ የመታደድሪያ ደንብ አሻሻይ ኮሚቴ አቋቁሞ ኮሚቴው ካሻሻቻለው በኋላ ሰበካ ጉባኤው የመተዳደሪያ ደንቡን አጥንቶ ፤ ምእመናን አሳትፎ ፤ አርሞና አቀነባብሮ ለምእመናን እንዲያጸድቁ ለ159 ቤተ ክርስቲያን አንድ ቀንም እንኳን ለመጡ ምእመናን ልኳል ፡ ከነዚህም 108 ምእመናን ባለቱን መልሰዋል። ከመለሱትም 96 ምእመናን መተዳደሪያ ደንቡን ተቀብለዋል ፤ 9 ምእመናን አልተቀበሉም 3 ባለት ውድቅ ሆኖአል። አቆጣጠሩም በሰበካ ጉባኤ በተመረጡ 2 ባለት ቆጣሪዎች ፤ አንድ ፀሀፊ ፤ አንድ ከመተዳደሪያ ደንብ አሻሻ ኮሚቴ ፤ አንድ ታዛቢ በተገኙበት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቆጥሮ Feb. 6, 2021መተዳደሪያ ደንቡ ጸድቋል።

በአንቀጽ 8-2 የአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ የሰበካ ጉባኤው ቋሚ ሰብሳቢ ይሆናል በሚለው መሰረት መልአከ ገነት ዳኛቸው ደገፉ የሰበካ ጉባኤው ሰብሳቢ ሆነው ከFebruary 15, 2021 ጀምሮ ስብሰባውን ማካሄድ ጀምረዋል።

ቤተ ክርስቲያን ለመግዛት በተወሰነበት ጊዜ የገንዘብ እጥረት ስለነበረ ሰበካ ጉባኤው ከአምስት ምእመናን እያንዳንዳቸው $10,000 በጠቅላላው $50,000, ተበድሮ እነዚህ ምእመናን በሁለት አመት ውስጥ እንዲከፈላቸው ውል ተፈራርሞ ነበር ። በ2021 ሰበካ ጉባኤው ይሄንን የ$50;000 ብድር ለመክፈል ችሏል።

ስማቸው መጠቀስ ያልፈለጉ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ሁለት ጊዜ ለአምስት ወር የሚሆን የሞርጌጅ ክፍያ እና አንደ ጊዜ የስድስት ወር የሞርጌጅ ክፍያ አድርገውልናል ለዚህም ስጦታቸው እግዚአብሄር ዋጋቸውን እንዲሰጥልን የበረከት እንዲያደርግላቸው መልካም ፈቃዱ ይሁን።

በቤተ ክርስቲያን ህግ መሰረት የህጻናቶቹና የታዳጊ ወጣቶች ትምህርት በሰንበት ትምህርት ቤት ስር እንዲጠቃለል ሰበካ ጉባኤ አድርጓል።

በAugust 9,2021 በጻፉት ቴክስት ሁለት የሰበካ ጉባዬ አባላት ዶ/ር መልአኩ ላቀውና አቶ ፀጋዬ አድማሱ ከአባልነት በፈቃዳቸው መልቀቃቸው ይታውሳል። በአንቀጽ 9-1 በሀመሩ ሐ ላይ መተዳደሪያ ደንቡ እንደሚፈቅደው ስራቱን ተከትሎ ሁለት ምእመናን ወ/ሮ ትግስት ዘገዬን በምክትል ሰብሳቢነት እና አቶ ወርቁ አከለ አባል ሆነዋል እንዲሁም ወ/ሮ ዓለም ፀሀይ ከበደ ተጠባባቂ አባል ሆናለች።

## <u>ቤተ ክርስቲያናችን አሁን ለደረስንበት መለያየት ምክንያቱ</u>

ብፁዕ አባ ፊልጶስ መልአከ ገነት ዳኛቸውን ቄስ በላይ አፍኔን አባርረሃልና ወደ ሥራው መልስ የሚል የሐሰት ደብዳቤ ታህሳስ 18, 2013 (12/27/20) ጽፈዋል።

መልአከ ገነት ዳኛቸው ለብፁዕ አባ ፊልጶስ ቄስ በላይ አፍኔ በራሳቸው ፈቃድ የቤተ ክርስቲያኑን ቁልፍ መልሰው ሄዱ እንጂ እኔ አላባረርኩም ስለዚህ ይህ ደብዳቤ ይነስሣልኝ በማለት በታህሳስ 18, 2013 (በ3/15/2021) በደብዳቤ አመልክተዋል ።

ለዚህ ደብዳቤ መልሱ አግጂሃለሁ የሚል በነሃሴ 24,2013 (8/24/21) ደብዳቤ እና ቁልፍ ማሰበርና ማዘጋት ለመልአከ ገነት ዳኛቸው ሳይደርስ ለፖሊስ ተሰጥቶ እሳቸው እዚህ እንዳይደርሱ ቤቱም የኔ ነው ብለው ቁልፍ አሰብረዋል።

በተጨማሪይም ነሃሴ 25,2013 (8/25/21) ከመተዳደሪይ ደንባችን ውጭ ሕገ ወጥ የቤተ ክርስቲይን ሰበካ ጉባዔ እና አስተዳዳሪ አድርገው ሾመዋል።

መልአከ ገነት ለብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ አቡነ ማትያስ ብፁዕ አባ ፊልጶስ ይነሱልን ብለው በ9/16/2021 አቤቱታ አቅርበዋል። ሰበካ ጉባዔውም ብፁዕ አባ ፊልጶስ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እንዳይመጡብን በ9/18/2021 በደብዳቤ ጠይቀዋል። ብፁዕ አባ ፊልጶስ ወ/ሮ ሄርሜላን አቶ አብነትን እና አቶ ብሥራትን ከሰበካ ጉባዔ አስተዳደር በ9/22/2021 በሐሰት ደብዳቤ አባረዋል።

**ከዚህ ቀጥሎ በቤተ ክርስቲያችን ውስጥ በብፁዕ አባ ፊልጶስ የሐሰት ደብዳቤ ምክንያት የተፈጠረው ችግር ዝርዝር ሁኔታ (ሪፖርት)እንዲህ ይቀርባል**

በደ/ገ/ቅ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን እና አስተዳደር ሰበካ ጉባኤ ውስጥ በተፈጠረው አለመግባባት ሶስት የሰበካ ጉባኤ አባላት የነበሩ ግለሰቦች በፈጠሩት ህገወጥ እንቅስቃሴ ማለትም አድማ በማድረግ፣ አስተዳደር ሰበካ ጉባኤው ለሁለት ተከፍሏል ብለው የተዛባ ወሬ በማሰራጨት የቤተ ክርስቲያን ህግና ደንብ በመተላለፍ አጠቃላይ ጉባኤ ጠርተው ከቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እውቅና ውጭ በዙም የተወሰኑ ጥቂት ግብረአበሮቻቸውን ሰብስበው የራሳቸውን አዲስ አስተዳደር ሰበካ ጉባኤ ብለው ምርጫ አድርገዋል።

በተጨማሪም አቶ ፀጋዬ አድማሱ ምክትል ሰብሳቢ የነበረ እና ዶ/ር መልአኩ  ላቀው ከሰበካ ጉባዔ ለቀው  ወጥተው ቤተ ክርስቲያን አፍራሹን ቡድን ተቀላቅለው በሕገ ወጥ መንገድ ምእመናን ለሞርጌጅ የከፈሉትን ገንዘብ ዘርፈው ወስደዋል። ዶ/ር  መልአኩ ገንዘቡን ለጊዜው አሳግዶ ቆይቶ  ከአስለቀቀ በኍላ አቶ ፀጋዬ አድማሱ ወዲያውኑ  በቼክ አውጥቶ ወስዷል በመመሳጠር የቤተ ክርስቲያን ሞርጌጅ ክፍያውን ዘርፈው ወስደዋል። ደግሞም ከቤተልሄም መስዋእት መስሪያ ማሕተም ተወስዷል።

በመቀጠልም በህጋዊ ደንብ የተመረጠውን የሰበካ ጉባኤ አስተዳደርን በሃይል ለማስወገድ ሴራ ጠንስሰው በ9/04/21 የቤተ ክርስቲያን በር ሰብረው በመግባት ቁልፎችን ሁሉንም በመቀየር በአስተዳደሩ እና በምዕመናኑ ላይ በር ዘግተው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን እንዲቋረጥ አድርገውል።

የተዘጋውን በር በህጋዊ መንገድ ጠበቃ በመያዝ እንዲከፈት አድርገናል። ለዚህም አንዳንድ ከቤተ ክርስቲያንና ከምዕመናን ትብብር ተደርጎ የገንዘብ ወጪ የሚጠየቀውን ሁሉ በማድረግ የተሳካ እንቅስቃሴ ተደርጓል። በሩን የሚከፍት ሎክስሚዝ በመጥራት በሮቹን በማስከፈት ቁልፎችም በአዲስ እንዲቀየሩ ተደርጓል። ለጸጥታ ስጋት እንዲረዳን በማሰብ፣ የሞርተን ፖሊስ በተለያዩ ግዜያት እንዳስፈላጊነቱ ጥበቃ እንዲያደርጉልን በአስተዳደር እየተወሰነ በሰዓት አበል ተከፍሏል። እንዲሁም፣ የሴኩሪቲ ጋርድ ባስፈለገ ግዜ ሁሉ ለጸትታ ጥበቃ በክፍያ በሰዓት አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል። በህንጻው ስርና በሮች ላይም የሴኩሪቲ ካሜራ ከምዕመናን እና ከአባላችን በዕርዳታ ተሰጥቶን የባለሞያ ክፍያ ወጪ በማድረግ እንዲገጠሙ ተደርጓል። በተጨማሪም የብሊንክ ካሜራ ከሆምዲፓ በመግዛት ባስፈላጊው ቦታዎች ተገጥመዋል።ሌላው የቤተ ክርስቲያኑ አላርም መቀየር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በአዲስ ካንፓኒ እንዲቀየር ተደርጓል። ለዚህም አስፈላጊ የሆነውን ወጪ ሁሉ ቤተ ክርስቲያኑ አድርጓል።

ይህንንም አድማ በበላይነት የመሩት ግለሰቦች እና ግብረአበሮቻቸው በፍርድ ቤት ክስ ስለመሰረቱብን የቤት ባለቤትነት ጥያቄ በማንሳት የይገባኛል ክርክር ተደርጓል። ለዚህም በቤተ ክርስቲያኑ በኩል ጠበቃ መያዝ ስለታመነበት ቀና በሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ከአስተዳደር ሰበካ ጉባኤው ጋር በመወያየት አስፈላጊውን ወጪ ከራሳቸው አዋጥተዋል። እንዳስፈላጊነቱም ከቤተ ክርስቲያን ወጪ ተደርጓል።

በጀነዋሪ 7, 2022 በተደረገው የፍርድቤት ውሎ ዳኛው ከተደጋጋሚ ቀጠሮ በኋላ የከሳሾች እና የተከሳሾች ማስረጃና የቃል ምስክርነት ተደርጎ ክሱን ውድቅ አድርጎታል። በመሆኑም እነዚህን አድመኞችና ተባባሪዎቻቸውን ቤተ ክርስቲያን ግቢ ድረስ እየመጡ የጸሎት አገልግሎቱን በመረበሻቸው በጠበቃችን በኩል የእገዳ ደብዳቤ ተጽፎላቸዋል። ተባባሪዎቹም ከአባልነት እንዲሰረዙ ተደርጓል።

ውስብሐት ለእግዚአብሔር

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

## በደብረ ገነት ቅዱስ አማኑኤል ወኪዳነ ምህረት ሰ/ት/ቤት አመታዊ ሪፖርት

በኮቪድ ምክንያት በአካል በቤተ ክርስቲያን ተገኝተን ማገልገል ስላልቻልን በየሳምንቱ በዙም ሰንበት ተማሪውን መዝሙር በማስጠናት በዙም

በሚሰጠው አገልግሎት ሰንበት ተማሪውን በየሳምንቱ እና በየወሩ እየመደብን አገልግሎት ስንሰጥ የቆየን ሲሆን ቤተ ክርስትያን ሲከፈትም በአካል

ተገኝተን የዝማሬ እና የተለያዩ አገልግሎቶችን እየሰጠን እንገኛለን።

በዚህ አመት ከአባላት ወርኃዊ መዋጮ የተሰበሰበ $700 ለደብራችን ገቢ አድርገናል፡፡

ለሰንበት ት/ቤቱ የተገዛው ከበሮ የተሰበር ስለነበረ ከበሮው ተመልሶ ገንዘቡ ተመላሽ ሆኗል፡፡

የህጻናት ክፍልም ህፃናቱን መዝሙር በማስጠናት በየሳምንቱ እሁድ እና በወር ሁለት ጊዜ ያቀርባሉ

የአባላት ቁጥራችን በተለያየ ምክንያት እየቀነሰ ይገኛል ስለዚህም ያሉንን አባላት ማጽናት እና ሰ/ት/ቤቱን ማጠናከር ላይ እና ታዳጊ ወጣቶችን
ወደ ሰንበት ትምህርት ቤቱ እንዲያገለግሉ እየሰራን እንገኛለን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

<u>2021 የዕቅድና ልማት (የፋይናንስ) ኮሚቴ ሪፖርት</u>

የዕቅድና ልማት ኮሚቴ በ2021 ሶስት ስብሰባዋች አድርጎል፦ ማርች 31 ቀን፣ኤፕሪል 14 ቀን፣እና ሜይ 26 ቀን

አቶ ጸጋዬ አድማሱ በጠየቁት መሰረት፣ ወ/ሮ ትእግሥት ዘገዬ የፋይናንስ ኮሚቴው ሰብሳቢ ሆነው ለማገልገል የቀረበላቸውን ጥያቄ መቀበላቸውን አስመልክቶ አባላት በሙሉ ሃላፊነቱ ወደ ወ/ሮ ትእግስት መተላለፉን ተቀብለውታል።

በአሁኑ ጊዜ $100 ወይም $50 ዶላር የሚያዋጡ ምእመናን ይህንን የተቀደሰ ተግባራቸውን እንዲቀጥሉበት ለማድረግ  የሰበካ ጉባኤው ማሳሰቢያ እንዲያስተላልፍ የፋይናንስ ኮሚቴው ጠይቆ በስራ ላይ እንዲውል አድርጓል።

የፋይናንስ ኮሚቴ አበላት ቁጥር ቀድሞውኑ ወደነበረበት ተመልሶ ሰባት (7) አባላት እንዲኖሩት ለማድረግ፣ አዲስ ሁለት (2) አባላት መጨመርን የሰበካ ጉባኤው የሚተኩበትን ሁኔታ እንዲያመቻችልን የፋይናንስ ኮሚቴው ጠይቋል።

ልዩ ልዩ ስዕሎች፣ ልብሶችና መጸሃፎች ለምዕመናን ሽያጭ አቅርቧል።

ምዕመናንን የቁሳቁስ መዋጮ ለቤተ ክርስቲያናችን እንዲያበረክቱ ጠይቋል።

የአምባሳደር ዘውዴ ረታ ቤተ ሰቦች በስጦታ ለቤተ ክርስቲያናችን የለገሱትን መጽሃፍቶች ለሽያጭ አቅርቧል።

የፋይናንስ ኮሚቴ እቃዎችን የምናስቀምጥበት አንድ ቁልፍ ያለው ክፍል እንዲያዘጋጅልን ጠይቋል።

መልአከ ገነት እነዚህን እቃዎች እየተመለከቱ፣ የትኞቹ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሸጥ እንደሚችሉ አሳውቀውናል።

የምዕመናን ቁጥርና ስንት ሰው $20 ወይም $30 እንደሚከፍል ሰበካ ጉባኤው እንዲያሳውቀን ተጠይቋል።

የፋይናንስ ኮሚቴው ስምፕ ፕምፕ (sump pump) ገዝቶ የሚያስፈልገውን ስራ እንዲሰራ እና በተጠናቀቀው ስምፕ ፕምፕ (sump pump) ፕሮጀክት ላይ ኮሚቴው $900 አበርክቷል።

የፋይናንስ ኮሚቴ የቤተክርስቲያኗን ከምዕመናን የተበደረውን $50,000.00 ብድር ለመክፈል አቅዷል። በዚህ እቅድ መሰረት $15,000 ለቤተክርስቲያኑ አስገብቷል።

የዕቅድና ልማት ኮሚቴ ለኢትዮጵያ ቀን ልዩ ልዩ ቁሳቁስ፣ ስዕሎች፣ ልብሶችና መጸሃፎች ለሽያጭ አቅርቧ $1906 ለቤተክርስቲያኑ አስገብቷል።

ውስብሐት ለእግዚአብሔር

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን!**

**<u>የ2021 ደ.ገ. ቅ.አማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ የህንፃ ጥገናና እድሳት ሪፖርት</u>**

**በ2021 የአገልግሎት ዘመን የተከናወኑ ክንውኖች መካከል፥**

**የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ በተመለከተ በውስጠኛው ክፍል ከሚገኙ የማሞቂያ እና ማቀዝቀዣ ወይም ሂተር እና ኤሲ ተብሎ የሚታወቀው ክፍል ለብዙ ዓመታት ያገለገሉ ሲሆን በዚህ ምክንያት በተደጋጋሚ ባለሞያ በመጥራት ጥገና እየተደረገ ቆይቷል**

**1ኛ .በJanuary 19-21 ማሞቂያው አልሰራ ብሎ በባለሞያ እንዲታይ ተድርጓል ከዚህ በኋላም በሚቀጥሉት ቀናትም በባለሚያ ታይቷል፥**
**በJanuary 20፣ 2021**
**በAugest 29፣ 2021**
**በNovemeber 10፣ 2021**
**በNovemeber 25፣ 2021**
**በDecember 19፣ 2021**

**የቲክኒክና የማቴርያል ጠገና በማድረግ የቤ/ክርስቲያኑን አገልግሎት ለምእመናኑ ዓስፈላጊውን ሰርቪስ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያኑ ጣሪያ በከችኑ መግቢያ በኩል በክረምት ዝናብ ሲዘንብ የማንጠባጠብ ችግር አጋጥሞት ለዚህም የጥገና አገልግሎት ተደርጓል።**

**ከዚህ በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያኑ የአስተዳደር ሰበካ ጉባኤ አባላት ከምዕመናን ጋር በመተባበር በራሳቸው ወጪ በማድረግ የፅዳትና የሳር ማጨድ እንዲሁም በክረምት የበረዶ ጠረጋ በግል ተነሳሽነት በግልም በህብረት ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረጋቸውን የሚዘነጋ አይደለም። ለዚህም አገልግሎታቸው እግዚአብሔር ዋጋቸውን እንዲሰጥልን የበረከት እንዲያደርግላቸው መልካም ፈቃዱ ይሁን።**

**በቀጠያም ዓመት የቤተ ክርስቲያኑ የውጭ እና የውስጥ ህንፃ ክፍል ዘላቂ እድሳት ከማድረግ በተጨማሪ የምእመናኑ ተሳትፎ በማስተባበር መሰረታዊ ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን ክፍል የማሞቂያና የማቀዝቅዣ ሰይስተም በተሻለ ዘመናዊ ቋሚ እቃዎች ለውጥ ቢደረግላቸው ለህንፃውም በወጪም በኩል መፍትሄ አስፈላጊ ነው ለምእመናን ማስገንዘብ እንፈልጋለን**

**ውስብሐት ለእግዚአብሔር**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

## በአማኑኤል ወኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን የሕግ ጉዳይ

በOctober 6, 2021 የቀጠሮ ደብዳቤ በ10/20/21 በ11፡00 am ፍርድ ቤት እንድንገኝ ደርሶናል።

በSeptember 22, 2021 በRonald A Smith አማካይነት መልአከ ገነት ዳኛቸው በመሪጌታ ዓባተ በአቶ ፀጋዬ አድማሱ እና በአቶ አሳምነው ዲልቡ ተከሰዋል ። ክሱ በ9/27/21 መልአከ ገነት ከቤተ ክርስቲያን ለጊዜው ወይም ለዘለቄታው እንዲወጡ የሚል ነው።

በOctober 15, 2021 የእኛ ጠበቃ ክሱን የሚቃወም ደብዳቤ ከነማስረጃው ለፍርድ ቤት አስገብቷል ። ከሳሾች ያስገቡትን ክስ amend አድርገው አስገብተውታል። በዚህ ክስ ላይ አቶ በለው አስፋ እና አቶ ጌትነት ግድየለው ተጭምረዋል።

የመጀመሪያው ክስ የሚያሳየው 1) መልአከ ገነት ዳኛቸው ከአስተዳደር እንደተሻሩ 2) መርጌታ ጊዝዊ አስተዳዳሪ እንደሆነ 3) ቤተ ክርስቲያኑ የሚመራው በቃለ አዋዲ እንደሆነ ሲሆን Amend የተደረገው ክስ እነዚህን 3 ጉዳዮችን እንዳለ አድርጎ ሌላ ሁለት ክሶች ጨምሯል። ይህውም 1) ጳጳሱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነት ሀላፊነት እንዳለባቸው 2) ቤተ ክርስቲያኑ ለከሳሾች እንዲመለስ የሚል ነበር

በNovemeber 19, 2021 የእኛ ጠበቃ Amend ለተደረገው ክስ መልስ ሰጥቷል። በJanuary 7, 2022, ተከሳሾች ፍርድ ቤት ቀርበን ለብዙ ሰአታት በዳኛ ፊት እራሳችንን ለቀረበልን ክስ መከላከያ አቅርበናል።

በJanuary 10, 2022, ፍርድ ቤቱ ለኛ ፈርዶልን በህጋዊነት ቤተ ክርስቲያኑን ማስተዳደር ቀጥለናል

---

## በድሮ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን የህግ በተመለከተ

የሰበካ ጉባኤው ልዩ ኮሚቴ አቋቁሞ ሕጉን እንዲከታተል አድርጓል። የሕግ ኮሚቴ አባሎችም ወ/ሮ ትግስት ዘገዬ ፤ ወ/ሮ ሄርሚላ አባተ እና አቶ አብነት በየነ ሲሆኑ ፤ በተጨማሪም አቶ ኤፍሬም ካባ እና ዶ/ር ቅጣው ነጋሽ አብረው እንዲሰሩ ተመድበዋል።

ኮሚቴው በመጀመሪያ ከጠበቃው ከዊል ሩብሊ ጋር ስለ ሕጉ ጉዳይ በጥልቅ ተወያይቷል።

በSeptember 24, 2021 ተከሳሾች (Respondents) የፍርድ ቤቱ ጉዳይ Dismiss እንዲሆን ያቀረቡት አቤቱታ በፍርድ ቤቱ Denied ሆኖአል። ፍርድ ቤቱ ከሳሾች መጀመሪያ ያስገቡትን ጉዳይ Amend (አሻሽለው) ማስገባት እንደሚችሉ አስታውቋል።

በጊዜው አቶ ታፈሰ ወልዴ መልአከ ገነትን እና ወ/ሮ ሄርሚላ አባተን ከከሳሾች ውስጥ አስወጥቶ ጉዳዩን አሻሻሎ) Amend አድርጎ አስገብቷል።

በመስከረም ወር በአለንበት ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ችግር የተፈጠረበት ወቅት በመሆኑ ዳኛው ጊዜ እንዲሰጠን ጠይቀናል በመሰረቱም ዳኛው 90 ቀን ወይም እኛ በተዘጋጀን ጊዜ ጉድዩን ለመቀጠል ተስማምቷል;

ይህ በንዲህ እያለ አሁንም ተከሳሾች ክሱ dismiss ይሁንልን ብለው ለዳኛው በጠበቃቸው በኩል ደብዳቤ አስገብተዋል። እስካሁን ከፍርድ ቤቱ የሰማነው ነገር የለም።

ውስብሐት ለእግዚአብሔር

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

## የኮቭድ የጤና ኮሚቴ ጠቅላላ ሪፖርት

እንደሚታወቀዉ ይህ የጤና ኮሚቴ በሰበካ ጉባኤዉ አስተዳደር ተሰይሞ ስራ መስራት ከጀመረ ከአመታት በላይ ሆኖታል። አባላቱ በተለያዩ ጊዜአቶች በመሰብሰብ አስፈላጊዉን የኮቭድ መከላከል አድርገዋል። የጤና ኮሚቴዉ አስፈላጊዉን ጥንቃቄ በማድረጉና መሟላት ያለባቸዉን ነገሮች በቅድመ ሁኔታ በማሟላቱ ምእመናን በተቻለ መጠን እራሳቸዉን ከበሽታ ለመከላከል ከፍተኛ የሆነ ጥረት አድርገዋል። ቤተ ክርስቲያኑ ከመከፈቱ በፊት አስፈላጊ የሆነ ቅድመ ጥንቃቄ ተደርጎአል። ለምሳሌ ያክል የአካባቢዉን የጤና ድርጅት (CDC guideline) በመመልከት እና የሚያዛቸዉን ትእዛዞች በደንብ በመጠበቅ የመጀመሪያ ሥራችንን በጥንቃቄ ጀምረን በተቻለን መጠን ምእመናኑን ከዚህ አስከፊ ወረርሽኝ እራሱን እንዲጠብቅ ግንዛቤን ሰጥተናል። የትምህርቱም አሰጣጥ የነበረዉም ዘመኑ በፈቀደዉ ቴክኖሎጂ በዙም ስለነበረ ወንድማችን እና የኮሚቴአችን ሰብሳቢ አቶ አብነት (ነርስ) የትምህርት ገለጻዉን በሚገባ በተደጋጋሚ አብራርቶ ለምእመናኑ እንዲደርስ አድርጎአል።

ለምእመናን ከተሰጡት ግንዛቤዎች መካከል

- አፍና አፍንጫን መሸፈን
- አካላዊ እርቀትን መጠበቅ
- እጅን በሳሙና መታጠብ
- በሃንድ ሴኒታይዘር እጅን መጠራረግ
- አንድ ምእመን የበሽታዉ ምልክት ሲታይበት ምን ማድረግ እንዳለበት
- አንድ ምእመን በሥራ ምክንያትም ይሁን በሌላ መልኩ በሽታዉ በዛ ወዳለበት አከባቢ ከሔደ ወደ መኖሪያዉ በሚመለስበት ሰአት ለ14 ቀናቶች እራሱን ከሌላዉ ህብረተሰብ መለየት እንዳለበት
- ህፃናት እና ከ12 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች መምጣት እንደሌለባቸዉ ይሁንና ወላጆች ልጆቻቸዉን ቅዱስ ቁርባን ማቁረብ ከፈለጉ አንድ ቤተሰብ ብቻ በሳምንት ተራ በመግባት ልጆቻቸዉን ማቁረብ እንደሚችሉ ግንዛቤ ተሰጥቶአል

ቤተ ክርስቲያኑ ከመከፈቱ በፊት የተደረጉ ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር

- የሚመጡትን ምእመናን ቁጥር በCDC guideline መሰረት መወሰን
- ምዝገባ ማድረግና ሲመጡም በተዘጋጀላቸዉ ወንበር ላይ ማስቀመጥ
- ምእምናኑ በሚመጡበት ሰአት የየራሳቸዉ የሆነ ቁጥር ይሰጣቸዋል
- የተሰጣቸዉን ቁጥር ይዘዉ ዘወትር የተወሰነላቸዉ ወንብር ላይ ይቀመጣሉ
- አካባቢያቸዉ ያለዉን ሰዉ በደንብ ማጤን ይኖርባቸዋል ይሄም የሆነበት ምክንያት ድንገት እንኳን አጠገባቸዉ የተያዘ ሰዉ ካለ ለኮንታክት ትሬሲንግ ይረዳን ዘንድ ነዉ
- ምንም አይነት የሻይና የዳቦ መስተንግዶ እንደቀድሞዉ መደረግ እንደሌለበት ወስነናል
- Hand sanitizer, disinfectant, ማስክ የመሳሰሉትን አዘጋጅተናል
- በበጎ ፈቃደኝነት የተወሰኑ ምእመናን በየግላቸዉ ማስክ, ሳኒታይዘር እና ማፅጃ ቁሳቁሶችን በማቅረብ ተባብረዋል

ክትባቱን አስመልክቶ የቀረበዉ ገለጻ

ክትባቱን አስመልክቶ በደንብ ገለጻ በወንድማችን በአቶ አብነት CRNP በደንብ ማብራሪያ ተሰጥቶናል። በሽታዉ አዲስ እንደመሆኑ መጠን ክትባቱም አዲስ ስለሆነ በሌሎችም ይሁን በኛ ሶሳይቲ ላይ ከፍተኛ የሆነ ብዥታን አሳድሮ ነበር። ነገር ግን የተለያዩ databaseዎችን በማስደገፍ አቶ አብነት በደንብ ማብራሪያ ሰጥቶበታል። ክትባቱን ለመዉሰድ ማንም ሰዉ ግዴታ እንደሌለበት እና የጤና ኮሚቴዉም ማንንም ሰዉ በማስገደድ ክትባት አዲወስዱ ግፊት አላደረገም።ይሁን እንጂ ክትባቱን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የት መጠየቅ እንዳለባቸዉ፤ እንደገናም ደግሞ ስጋት ካለባቸዉ የግል ሐኪሞቻቸዉን ማማከር እንዳለባቸዉ፤ ክትባቱን መዉሰድ ለነሱ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ሰቦቻቸዉና ለአካባቢዉ ህብረተሰብ በሽታዉን በመከላከል ብዙ ውጤት እንዳለዉ ተነግሮአል።

- ክትባቱን መከተብ ጠቃሚ እንደሆነ
- ክትባቱ ሙሉ በሙሉ በሽታዉን ማስወገድ ሳይሆን ህመሙን መቀነስ እንደሚችል
- ክትባቱ ዉጤታማ መሆኑን እና የተከተቡ ታማሚዎችን ቁጥር መቀነሱን
- ክትባቱን የወሰደ ማንኛዉም ሰዉ ቤተ ክርስቲያን በሚመጣበት ሰአት ማስክ ማድረግ እንዳለበት

በተጨማሪም ዶ/ር ገበየሁ ተፈሪን በመጋዝ ሰፋ ያለ ትምህርት ለምእመናን ተሰጥቶአል። ለምሳሌ አብዛኛዉ አብያተ ክርስቲያናት ማለትም እኛ ካለንበት አከባቢ ዉጪ ያሉት ማለት ሲሆን በበሽታዉ እንደተጠቁ እና እኛም አስፈላጊዉን የሆነ ጥንቃቄ መዉሰድ እንዳለብን ሰፋ ያለ ግንዛቤን አስጨብጠዉናል። ስለማስክ አደራረግ፤ ስለክትባት ጠቀሜታዉና አስፈላጊነቱም ማብራሪያ ሰጥተዉናል። ከምእመናን በተነሳላቸዉ

ጥያቄዎች ላይም ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ አገልግሎት ተጀምሮም ብዙም ሳይቆይ እንደገና ወረርሽኙ በመጨመሩ ሳቢያ ቤተ ክርስትያን ለምእመናን ዝግ ሆና ሁሉም ነገር በዙም እንደገና መተላለፍ ጀመረ። ከጥቂት ወራቶች በኋላ በምመናን ከፍተኛ ጥያቄ እንደገናም አብዛኛዉም ባይሆን ጥቂት ክትባቱን በወቅቱ የተከተቡ ምእመናን ስለነበሩ ለሁለተኛ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን ለምእመናን ክፍት ሆና አገልግሎት መስጠት ጀመረች። ነገር ግን ለሁለተኛ ጊዜ በሚከፈትበት ሰአት ከበፊቱ የበለጠ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ስለተረዳን የሚከተሉትን ሃሳቦች አቅርበናል

- የሚመጡትን የምእመናን ቁትር ቀንሰናል
- ቅዳሴን እና ኮቭድን በተመለከተ ለአባቶች ሀሳብ አቅርበናል
- አረጋዉያን እንዲሁም የተለያየ አይነት የህመም ችግር ያለባቸዉ ወረርሽኙ እስከሚያልፍ ድረስ እቤት በመሆን በዙምም ወይም በስልክ መሳተፍ እንዲኖርባቸዉ ተደርጓል
- ወጣቶች እና አረጋዊያን ወይም (pre existing medical condition) ያለባቸዉ በአንድ ላይ እንዳይቀመጡ አድርገናል። ምክንያቱም ወጣቶች ብዙዉን ጊዜ የህመሙ ምልክት ስለማይታይባቸዉ መዘናጋትን ይፈጥራል
- ቤተ ክርስቲያኑ ዉስጡ ስለማይበቃ አገልግሎቱ እዉጪ ላሉት ምእመናን እንዴት በፕሮጀክተር ወይም በቴሌቭዥን እስክሪን መተላለፍ እንዳለበት ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ይመጡ የነበሩ ጥቂቶች ስለሆኑ ይሄኛዉ የአገልግሎት መንገድ አላስፈለገንም ነበር ቤተ ክርስቲያንም በሚመጡበት ሰአት ከምን ጊዜዉ በበለጠ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ተደርጎ ነበር። እንደምሳሌ ብንጠቅስ,
    - የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ማድረግ ግዴታ ነበር
    - የ 2 አመት ወይም ከዛም በታች ያሉ ህፃናት የአፍንጫ ወይም የአፍ መሸፈኛ ማድረግ አይፈቀድም ነበር
    - ማስክ ላልያዙት ወይም ላላደረጉ ምእምናን ማስክ እንዲሰጥ አድርገናል
    - የእጅ ማፅጃ ወይም (hand sanitizer) አቅርበናል
    - ሙቀታቸዉ እየለካን ሙቀታቸዉ  ኖርማል የሆኑትን ብቻ አስገብተናል
    - በሚስሉበት ወይም በሚያስነጥሱበት ሰአት አፍና አፍንጫቸዉን መያዝ እንዳለባቸው ግንዛቤን ሰጥተናል
    - የተጠቀሙበትን ናብኪን ወደተዘጋጀዉ የቁሻሻ መጣያ መጣል እንዳለባቸዉ መክረናል
    - እጃቸዉን በደንብ አድርገዉ መታጠብ እንዳለባቸዉ
    - እቤታቸዉ አንድ ታማሚ እንግዳ ከመጣ እነሱም ቢያንስ ለ14 ቀን ከቤተ ክርስቲያን እራሳቸዉን ማግለል እንዳለባቸዉ አስረድተናል

ፅዳቱን በተመለከተ

ቢያንስ በተወሰነ ጊዜ አንዴ በባለሙያዎች (professional) መፅዳት አለበት ብለን ተወያይተን ነበር ይሁን እንጂ ባለሙያዎች መጥተዉ ያጸዱበትን ቀን አናስታዉስም። ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በኋላ የተወሰኑ የጤና ኮሚቴዎች መልካም ለመስራት ፈቃደኛ ከሆኑ ምእመናን ጋር አብረዉ በመሆን የቤተ ክርስቲያኑን ፅዳት ቀጥ ብለዉ በማጽዳት እነሆ እስከዛሬ ድረስ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ሆኖም ግን አንዳንዶቻችን በሥራም ምክንያት ይሁን በምን እነኚህ የጤና ኮሚቴዎች ለመርዳት አልቻልንም።

የጤናዉ ኮሚቴ ያጋጠሙት ተግዳሮቶች

በሲዲሲ መመሪያ መሰረት በማስክ አደራረግ ላይ ትንሽ የጥንቃቄ ጉድለት ታይቶ ነበር፤ አካላዊ ርቀትንም በመጠበቅ ላይ ትንሽ ክፍተቶች ታይተዋል፤ ይሁን እንጂ እስከአሁን ድረስ ማንም አባሎቻችን በእግዚሐብሄር ቸርነት ለክፉ አልተጋለጡብንም። ወደፊትም ቤተ ክርስቲያኗ በምትፈልገዉ መጠን የጤና ኮሚቴዉ አስፈላጊዉን አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ነዉ።

## ውስብሐት ለእግዚአብሔር